# የማያንቀሳቅሱ አዋጆችን በማፅደቅ ዲሞክራሲያዊ አገር መገንባት አይቻልም

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በርካታ ሕጎች፣ ስምምነቶች፣ አዋጆች፣ በጀቶች፣ … ይፀድቃሉ። ሁሉም ግን በተቃዋሚዎች ወይም ደግሞ በባለጉዳዩ ተቃውሞ አይገጥማቸውም። አንዳንዶቹ እንደውም መጽደቃቸውን ማንም ቁብ ሳይላቸው ድምፀ ተአቅቦ ከሚያሰሙት በስተቀር ሁሉም እጁን አውጥቶ ያፀድቃቸዋል።

ሰሞኑን ግን አወዛጋቢ የሆኑ አዋጆች በፓርላማ እየፀደቁ ናቸው። አንድ አዋጅ ሲወጣ ሕግ ሆኖ ለመዳኘት እንዲያገለግል እንጂ የዜጎችን ነፃነት ሆን ብሎ እንዲያፍንና እንዲገድብ ታስቦ መሆን የለበትም።

የምርጫ አዋጅ በፓርላማ ከመፅደቁ በፊትና ሊፀድቅ ሲል ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሻሻልላቸው አበክረው ጠየቁ፤ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ሳያገኝ በመጀመሪያው ረቂቅ ላይ ከቃላት ለውጥ በስተቀር ብዙም ማሻሻያ ሳያደርግበት ፀደቀ።

ለአንድ አገር ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን በቀዳሚነት አስተዋፅኦ የሚያደርገው ተቋም ምርጫ ቦርድ ነው። ይህን ተቋም ሊገዛ የሚችል አዋጅ ሲወጣ ተወደደም ተጠላም በህዝብ ፊርማ ተደግፈው የተቋቋሙ ፓርቲዎች ሕጉ እንዲሻሻል ሲጠይቁ ጆሮ ዳባ ልበሱ ተብለው እንዲፀድቅ መደረጉ የኢህአዴግን "እኔ ያልኩት ካልሆነ …" የሚለውን አገዛዙን ይበልጥ ያጎላዋል። መንግሥት አድማጭ፣ አስተዋይና ቻይ መሆን አለበት እንጂ፣ "እኔ ያረቀቅኩትን ሕግ አፀድቃለሁ።" ማለት ፍፁም ማን አለብኝነት ነው።

በዚህ ሣምንት ደግሞ ምክር ቤቱ "የመገናኛ ብዙኀንና የመረጃ ነፃነት ረቂቅ ሕግን" አጽድቋል። የጉዳዩ ባለቤቶች እንደምናውቀው በዚህ ረቂቅ ላይ "በፓክት" አማካኝነት በተደረጉ ውይይቶች በርካታ አንቀፆች እንዲሻሻሉ ተጠይቋል። ጉዳዩ የሚመለከታቸው በሙሉ የማሻሻያ ሃሳብ አቅርበዋል። "የፕሬስ ሕጉ፣ በሕገ መንግሥቱ የተሰጡ መብቶችን ይነፍጋል፣ አፋኝ ነው፣ ፈሪ ያደርጋል ስለዚህ ሊሻሻል ይገባል" የሚሉ ውይይቶች ተደርገዋል። "ጆሮ ዳባ ልበስ" በሚል ብቻ የቃላት፣ የፊደልና የዓረፍተ ነገር ማሻሻያ ብቻ ተደርጎበት እንዲፀድቅ ተደረገ።

የጉዳዩ ባለቤቶች ይሻሻልልን በሚል እየጮሁ፣ ሕጉን ማፅደቁ መንግሥት ከህዝብ ጋር መደማመጥና መነጋገር አለመፈለጉን ያሳያል። አሁንም ይሄ የእኔ አውቅላችኋለሁ አባዜ ጥላውን አጥልቶ፣ በዚህ መንገድ በክርኔ ተጭኜ ነው የምገዛችሁ፣ በሚል ሽፋን አክርሮ ሕጉ እንዲፀድቅ ተደርጓል። ይህ መንግሥት በራሱ ሚዲያ ኢትዮጵያ የልማት፣ የሠላምና የዲሞክራሲ አገር ናት በሚል የሚናገረውን ራሱ በራሱ አፈርድሜ ያስገባዋል።

አሁንም የብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ፤ ባንኮችንና የባንኮች ማኅበራት ባደረጉት ውይይት ሕጉ ቢፀድቅ ተፅእኖና ችግር ሊያመጡ ይችላሉ ያሏቸውንና ሕገመንግሥታዊ መብት ጥሰት ናቸው በሚል የዘረዘሯቸውን አንቀፆች ይዘው ሕጉ እንዳይፀድቅ መንግሥትን ተማፀኑ። ነገር ግን ተማጽኗቸው ምንም አድማጭ ሳያገኝ፣ ማሻሻያ ሳይደረግባቸው በተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀየሩ ተደርጓል።

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማኅበራትን ለማስተዳደር የወጣው ረቂቅ አዋጅም በርካታ "አፋኝ ናቸው" የተባሉ አንቀፆች እንዲሰበሰቡ በርካታ መያዶች ተሰባስበው አጠብቀው ቢቃወሙም "እንናገር ካላችሁ ተጨማሪ ዕድል እንሰጣችኋለን ግን በጠቀሳችኋቸው አንቀፆች ላይ የሚቀየር ነገር አይኖርም" የሚል ምላሽ ተሰጥቷቸዋል። ስለዚህ መንግሥት የጉዳዩ ባለቤቶች "ዲሞክራሲያዊ አይደለም፣ የህዝብን ሕገ መንግሥታዊ መብትና ነፃነት የሚጋፉ ናቸው" እያሉ የሚጮሁባቸውን ረቂቅ ሕጐች ማፅደቁ ከህዝብ ጋር ተቀራርቦ ለመሥራት ያለውን ቁርጠኝነት አያሳይም።

ይልቁንም በቀጣይ ህዝብ ላይ ጫና በማሳደር በተለያዩ ሕጎችና አንቀፆች እንዳይፈናፈን ለማድረግ የታሰበ ይመስላል።

መንግሥት በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ዳብሯል በማለት ጠዋትና ማታ በመንግሥት ሚዲያ እየለፈፈ ከማሰልቸት ይልቅ፣ እንደዚህ አይነት አፋኝ ሕጎችን ከማፅደቁ በፊት በንፁኅ ልብና በንፁኅ ሕሊና ከጉዳዩ ባለቤቶች ጋር ሊወያይ ይገባል።

ሕጎችና አዋጆች ፀደቁ ማለት "አይቀየሩም" ማለት ባለመሆኑ አሁንም ቁርጠኝነቱ ካለ፣ የህዝብን ሕገመንግሥታዊና መብቱንና ነፃነቱን ሊጋፉ የሚችሉ አንቀፆችን ከባለ ጉዳዮቹ ጋር ተነጋግሮ ያስተካክል!